# Centrepay - ያለብዎትን የአገልግሎት ሂሳብ በCentrelink በኩል ስለመክፈል



We speak your language ☎ 13 1202

*Centrepay - Paying your bills through Centrelink* - **Amharic**

## Centrepay ማለት ምን ማለት ነው?




Centrelink ከሚሰጥዎት ገንዘብ እየተቆረጠ ያለብዎትን አንዳንድ የአገልግሎት ሂሳብ Centrelink በቀጥታ ሊከፍልሎት ይችላል። ይህም ምንም ገንዘብ የማይከፍሉበትና በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመረኮዘ ነው።

## Centrepay የሚሰራው እንዴት ነው?

ለሚከተሉትና ተመሳሳይ ለሆኑ አገልግሎቶች ክፍያ Centrelink ከሚሰጥዎት ላይ ምን ያህል ተቀናሽ ሆኖ መከፈል እንዳለበት የገንዘቡን መጠን የሚወስኑት እራስዎ ኖት።

- የቤት ኪራይ
- የስልክ
- የኤሌትሪክ፣ የጋዝና የውሃ
- ለትምህርት ክፍያዎች
- ለአምቡላስ የወጣ ወጪ
- ለመዋእለ ሕፃናት
- በቤት ውስጥ ለሚሰጥ የክብካቤ አገልግሎት
- ከወለድ ነጻ ለሆኑ ብድሮች
- ለቤት እቃዎች ኪራይ ክፍያዎች ናቸው።

ገንዘብ ተቆራጭ እየሆነ የሚከፈለው በወቅታዊነት በCentrepay ለተመዘገቡ ድርጅቶች ብቻ ነው።

**ማሳሰቢያ፣** በCentrepay በኩል ለእያንዳንዱ ክፍያ የሚቆረጠው የገንዘብ መጠን በሁለት ሳምንት ከ$10 ዶላር ያላነሰ ይሆናል።

## ለምን Centrepayን መጠቀም ያስፈልጋል?

Centrepay ያለብዎትን ክፍያ አነስተኛና ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ሳይቋረጥ ከCentrelink ክፍያዎ እየተቀነሰ በቀጥታ እንዲከፈል ከማስቻሉም በላይ ሂሳብዎን ተቆጣጥረው ለመጠቀም ያስችሎታል።

በየወቅቱ የሚከሰተውን የሂሳብ ዝቅና ከፍ ማለት በCentrepay በኩል በቀላሉ ተቆጣጥሮ ማስተዳደር ይቻላል ይህም በክረምት ወራት ለሙቀት ሃይል ፍጆታ ወይም ደግሞ በበጋ ወራት ለማቀዝቀዝ የሃይል ፍጆታ ጭማሪ ይሆናል።

## ወጪ ያስወጣኛልን?

አያስወጣም፣ ይህንን አገልግሎት ለመጠቀም Centrepay ምንም ክፍያ አያስከፍልዎትም።

## በCentrepay በኩል የሚቀነሰውን ክፍያ ለማስቀረት ወይም የገንዘቡን መጠን ለመቀየር እችላለሁን?

አዎ ይችላሉ፣ Centrepay በፈቃደኛነት የሚደረግ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ የሚቀነሰውን ክፍያ ማቆም ወይም የገንዘቡን መጠን መቀየር ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው Centrelink ጽ/ቤት ስልክ በመደወል ወይም በመሄድ ሊያነጋግሩ ይችላሉ ወይም ደግም በዌብሳይት www.centrelink.gov.au ላይ በCentrepay በኩል የሚደረገወን ክፍያ መቀየር ይችላሉ።

## ምን ጊዜም ቢሆን በእራስዎ ገንዘብ የሚያዙት እርስዎ ኖት

በሚከተሉት ሂኔታዎች የተነሳ Centrepay የጠየቁትን ያህል የገንዘብ መጠን ሁሉ ለመቀነስ አይችል ይሆናል።

- ሌላ ገቢ ወይም ገንዘብ ሲያገኙ የሚከፈልዎት ክፍያ ስለሚቀንስ።
- ሌሎች ለCentrelink የግዴታ መክፈል ያለብዎት ጉዳይ ሲኖር ለምሳሌ በቅጣት ወይም ከሚገባዎት በላይ ስለተከፈሉ ያ እላፊ ክፍያ መመለስ ስላለበት፣ እየተቆረጠብዎት ከሆነ።

ይህ ሁኔታ ሲከሰት ከአገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር ልዩነቱን ለመክፈል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርብዎታል።

## ለCentrepay ማመልከት እንዴት እችላለሁ?

የፍጆታ ሂሳብዎን በCentrepay በኩል ለመክፈል በመጀመሪያ ከCentrelink ወይም እንዲከፈለው ከሚፈልጉት ድርጅት ጋር በመነጋገር በዚህ ረገድ መክፈል ይችሉ እንደሆነ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። በአቅራቢያዎ ወደ አለው Centrelink ጽ/ቤት በመደወል ወይም በመሄድ ሂሳቡ እየተቆረጠ እንዲከፈል ማድረግ ይችላሉ። እንዲሁም በዌብሳይት ላይ **www.centrelink.gov.au*** የCentrelink's የሽያጭ አገልግሎት የሚለውን ማየት ነው። በሌላ መንገድ የCentrepay መክፈያ የማመልከቻ ቅጽ መሙላት ይችላሉ።

***አባክዎን ያስታውሱ፡** ይህ አገልግሎት በእንግሊዝኛ ብቻ ነው የሚቀርበው።

**በራስዎ ቋንቋ በይበልጥ ለመረዳት 13 1202* ን ደውለው ይጠይቁ። በ ኢንተርኔት ድር፣ www.centrelink.gov.au መረጃ ማግኘት ይቻላል።**

** በ '13' ለሚጀምሩ ቁጥሮች ከቤትዎ ወይም የህዝብ ቴሌፎን ሲደውሉ ወጪው የአካባቢን ጥሪ ዋጋ ያህል ያስወጣል። ቢሆንም፣ የጥሪው ሂሳብ እንደ ቴለፎን አገልግሎቱ ድርጅት ዓይነት ሊጨምርም፣ ሊቀንስም ይችላል። በ '1800' ወደ ሚጀምሩ ቁጥሮች ከቤትዎ ወይም ከህዝብ ቴሌፎን ሲደውሉ የአካባበዎን ጥሪ ዋጋ ያስወጣዎታል። ከህዝብ ቴለፎንና ሞባይል የተደረገ ጥሪ ይበልጥ ያስወጣል።*